# "...የክህደት ውጤቱ ደግሞ ሞት እንደሆነ፣
# ከዶ/ር አብይ በላይ የሚያውቅ የለም።"

ተማም አባቡልጉ (አንጋፋ የህግ ባለሞያ)

April 20, 2018

ሕዝቡ የፈለገው "የሕዝብ ብሶት የወለደው አብይ አህመድ ኢሕአዴግን መንግስቱን እሱ ያለውንና ይጠቀምበት የነበረውን ሁሉ ለሕዝብ ጥቅም ተቆጣጥሮታል" እንዲባል ነው፡፡
የኢትዮጵያ ሕዝብ የሀገር ባለቤትነትን ከነገስታቱ ላይ በ 1966 ዓ ም አብዮት ቢያስጥልም ደርግ ቀማው፤ ሕወሃት-ኢሕአዴግን ሆኖ (ነኝ ብሎ) ደርግን ጥሎ የሕዝብ የሆነውን ነጠቀው፡፡

ሕወሃት-ኢሕአዴግ ግንቦት 1983 ዓ.ም እንዳለው ሳይሆን ሀገሪቷንና ያላትን ሁሉ ለራሱ ወሰደ እንጂ ለሁሉም ሕዝብ ጥቅም ተቆጣጥሮ ለሁሉም ባለማዋሉ ሆድ የባሰው ሕዝብ ብሶቱን ገለፀ፤ ይህም ሕዝባዊ ብሶትና ተቃውሞ ወደኢሕአዴግም ቤት ገባና ቲም ለማንና የዶ/ር አብይን መመረጥ ወለደ፤ ስለሆነም ባህሪያቸው፣ ድርጊታቸውና ንግግራቸው ይህንን ማሳየትና ማለት ያለበት ዶ/ር አብይ አህመድ በኢሕአዴግ መሪነት የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስቴርነትን ስልጣን ይዘዋል፤ የኢሕአዴግም የኢትዮጵያም መንግስት መሪና ወይም ዋና ስራ አስፈፃሚ ሆነዋል፡፡




ዶ/ር አብይ አህመድ እንደተለመደው፣ የከዚህ ቀደሙ ሁኔታ ኢሕአዴግ ዓላማውንና እምነቱ ወይም ፖሊሲውን ስራ ላይ እንዲያውሉለት የመረጣቸውና እሳቸውም ይህንኑ መስመር ብቻ ተከትለው የሚሰሩ እንደከዚህ ቀደምቶቹ ጠቅላይ ሚኒስትሮች አይደሉም፤ ሊሆኑም አይችሉም፤ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ሁሉ ከዚያ ፖሊሲ ተቃራኒ እንዲሰሩ የሚጠበቅባቸውም ናቸው፡፡
ኢህአዴግ ፖሊሲዬን ስራ ላይ የማዋል አቅም አላቸው በሚል የሾማቸውና ግዴታቸውም ይህንን የኢሕአዴግ ፖሊሲ ማስፈፀም እንደሆነው የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትሮች ዓይነት አይደሉም፤ ሊሆኑም አይችሉም፤ ስለሆነም ታማኝነታቸው ለኢሕአዴግ ፖሊሲ ሊሆን አይችልም፡፡
ዶ/ር አብይ ለኢሕአዴግም ሆነ ለኢትዮጵያ መሪነት የተመረጡት ሕዝቡ የኢሕአዴግን ፖሊሲዎች የችግሬ ምንጮች ናቸውና አልቀበልም፤ ኢሕአዴግም አይወክለኝም ወዘተ በማለቱና በእነዚህ ላይ ተቃውሞ በማንሳቱና የነፃነት፣ የእኩልነትና የፍትሓዊነት ጥያቄን ጨምሮ አጠቃላይ የሀገር ባለቤትነት ጥያቄ በማንሳቱ ይህንን የኢሕአዴግን ሕልውና በማስቀጠልና ፖሊሲውን ተግባራዊ በማድረግ መልስ ማግኘት የማይችለውን የሕዝብ ጥያቄ እንዲመልሱ ነው፡፡የሕዝቡ ጥያቄ የሚመለሰው ኢሕአዴግንና ፖሊሲውን በመቀየርና በሌላ በመተካት ነው። በትክክል በማስፈፀም አይደለም፡፡
ቢያንስ ቢያንስ የኢሕአዴግ አመለካከት አሰራርና አወቃቀር ለዚህ አዲሱ ሁኔታ እንዲመች ተደርጎ መሻሻል ይኖርበታል፤ ፖሊሲዎቹ ደግሞ ለዚህ አዲሱ ሁኔታ በሚያገለግሉ አዲስ ፖሊሲዎች መተካት ይኖርባቸዋል፤ ለዚያ እንዲያገለግሉ ተደርገው ሊሻሻሉ ይገባል። በበፊቱን እንደማያስፈፅሙ በግልፅ ሊነግሩንና ሊያረጋግጡልን ይገባል፡፡
ሕዝቡ "አሕዴድና ብአዴን አይወክሉንም፤ ኢሕአዴግ የኛ አይደለም፤ የኢሕአዴግ አወቃቀር የሕወሃትን እንጂ የሕዝቡንም ሆነ

ሕወሃት ያልሆኑትን አባል ድርጅቶችን ጥቅምና ፍላጎት ማስጠበቅ አይችልም፤ አድሎአዊ፣ አፋኝና ኢ-ዲሞክራሲያዊ ነውና …"የመሳሰሉ ጥያቄዎችን አቅርቧል፤ የተቃወመውም የኢሕአዴግን ሕልውና ነው፤ ፖሊሲዉን ብቻ ሳይሆን በብቸኝነት የሕዝብ ወኪል እንዲሆን የተደራጀበትንና ራሱን ያደረገበትን ሁኔታና መልክ ነው፡፡የሕወሃትን እስከዛሬ በጦርነት ላይ ያለ ይመስል ከነትጥቁና ስንቁ መቀጠል ነው፡፡

እንደሆነው ሆኖ፣ በሕዝብ አንፈልግህም ብቻ ሳይሆን ጎድቶናል (እየጎዳን ነው) የተባለን ድርጅት ሕልውናና ፖሊሲ ለማስቀጠል መስራት የሕዝብን ጥያቄ አልመልስም ማለት ስለሆነ ዶ/ር አብይ በዚህ ረገድ የአመለካከት ለውጥ በማምጣት መጀመራቸው ዝቅተኛው (ትንሹ) የመነሻ ነጥብ ይሆናል፡፡

በአጭር አነጋገር፣ ዶ/ር አብይ የኢሕአዴግን ፖሊሲ ማስቀጠልና ስራ ላይ ማዋልን በመተው አመለካከት ስራ መጀመር ይኖርባቸዋል፤ ይህ ማለት ደግሞ የሕዝብን ጥያቄ ለመመለስ የሚያስችል ሌላ ፖሊሲ በመቅረፅ ያንን ለማስፈፀም ስራ መጀመር ይኖርባቸዋል ማለት ይሆናል፡፡በኢሕአዴግ ውስጥ የኢሕአዴግ አባላትን ጨምሮ የሁሉም ሕዝብ ብሶት የወለዳቸው መሆናቸውን ሊረዱም ይገባል፡፡

ስለሆነም ዶ/ር አብይ ሕዝባዊ መሆናቸውን የምንረዳው ይህንን አመለካከት መሰረት ያደረገ ድርጊት መፈጸም ሲጀምሩ ወይም ይህንን የሚያንፀባርቅ ፖሊሲ ቀርጸው ለመተግበር እንደቆረጡ በግልፅ ሲነግሩንና እንደዚያ ሲፈፅሙ ነው፤ መፈፀም ሲጀምሩ ነው፡፡

እስከዚያውም የኢሕአዴግን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን፣ የውጭ ጉዳይ …ወዘተ ፖሊሲ ቢያንስ እንዳለ እንደማያስፈጽሙ ሊያረጋግጡልን ይገባል፡፡ ፡የኢሕአዴግን ፖሊሲ አስፈጽማለሁ!" ማለት ማቆም ብቻ ሳይሆን እንደማያስፈፅሙ በግልፅ ሊነግሩንና ሊያረጋግጡልን ይገባል፡፡




አዲስ የሚዲያና ኮሙዩኑኬሽን፣ የውጭ ጉዳይ፣ የመከላከያ፣ የፍትሕ፣ የባህል፣ የማኅበራዊ፣ የመሬት (የከተማና የገጠር መሬት አያያዝና አጠቃቀም) የግብርና የሴቶች የወጣቶች ወዘተ ፖሊሲዎች ያስፈልጓቸዋል፡፡

ካቢኔዎቻቸውንም ይህንን ሕዝባዊ ጥያቄ ለመመለስ የሚያስችሉትን ፖሊሲዎች ቀርፀው ለማስፈፀም በሚያስችላቸው መልክና ሁኔታ ማዋቀር ይጠበቅባቸዋል፡፡

በካቢኔ አባልነት መመረጥ ያለባቸው ይህንን አዲስ ሕዝባዊ ፖሊሲዎችን ተቀብሎ ለማስፈፀም ፍቃደኝነትና ፍላጎት ያላቸው እንጂ እንደከዚህ ቀደሙ የኢሕአዴግን ዓላማና ፖሊሲ ተቀብለው የሚያስፈጽሙ ሊሆኑ አይገባም፡፡

ኢሕአዴግም ለዚህ አዲሱ ፖሊሲ እንዲመች ተደርጎ መቀየር ይኖርበታል፤ ርዕዮቱና አደረጃጀቱ ለዚህ እንዲመች መሻሻል ይኖርበታል፡፡ ስለዚህ አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስቴር ኢሕአዴግን ለዚህ አዲሱ ፖሊሲያቸው መልካም አፈፃፀም በሚመች መልኩም ማዋቀር ወይም መምራት መቻል ይጠበቅባቸዋል፡፡

በነገራችን ላይ ሕወሃት ዶ/ር አብይን ያልመረጠው ይህንን የለጥው ሂደት ስለማይቀበል ሊሆን ስለሚችል በካብኔ አባላት አሰያየም ወቅት ይህ ከግምት ሊገባ ይገባል፡፡

ሕዝቡ ለኢሕአዴግ ያቀረበው ጥያቄ "በእኔ ስም እየማልክ በ 1983 ዓ ም የወሰድካቸውንና ለራስህ ጥቅም ያዋልካቸውን

ሀገሬን፣ ሀብቷንና ዕድሎቿን ከነወለዱ ከነሙሉ ክብሩና ኃላፊነቱ መልስልኝ" የሚል ነው፤ ይህ ግልፅ መሆን አለበት። ዶ/ር አብይ ኃላፊነታቸዉ ይህ ነው፡፡ ራሳቸውን፣ ኢሕአዴግን፣ ሀገሪቷን፣ ተቋማቷንና ሀብቷን ...ወዘተ በዚህ ግብ መሳካት በሚያመች መልኩም መቀየርም ይጠበቅባቸዋል፤ ሕዝቡም ሕዝቡንም እንደዚሁ፡፡

ኢሕአዴግ አሁን ሀገሪቷን ለሕዝቧ የመመለስን ሽግግር እንዲመራ በሚያስችለው መልክ በጊዜያዊነት መዋቀር አለበት፤ ለወደፊቱ ይህንን ሽግግር በሰላም ካሳካና ከዚያም የተነሳ በውለታነት በፓርቲነት የመቀጠል ዕድል ሊያገኝ ከቻለ፣ ለዚያ በሚያመች መልኩ በፓርቲነት መደራጀት ይገባዋል፡፡ ካልሆነ ይህንን ሽግግር መርቶ ለዚህም ከሕዝቡ የሚሰጠው ነገር ካለ ያንን ተቀብሎ መፍረስ ይገባዋል፡፡

ሕዝቡ አልቀበልም ያለው፣ አሁን ያለው ኢሕአዴግን፣ የፈጠራቸውን የሀገሪቷን ተቋማት ጨምሮ የመንግስትና የፓርቲውን የፖለቲካና ወታደራዊ አደረጃጀትና መዋቅር ስለሆነ መቀየር ያለባቸው ሁሉቱም ናቸው። እነዚህን የሕዝቡን ፍላጎትና ጥያቄ በሚያስጠብቅና በሚመልስ መልኩ ዳግም እንዲዋቀሩ የሚያስችል ሮድ ማፕና ፖሊሲ ሊወጣና ሊተገበር ይገባል፡፡

እነዚህን ለሕዝብ ብሶት በዘላቂነት መፍትሔ የሚያመጡትን አዳዲስ ፖሊሲዎችን በመቅረፅ ህዝብን ተቃዋሚዎችንና የሚመለከተውን ሁሉ አወያይቶ ለተግባር እንዲዘጋጅ የሚያደርግ አካል ማቋቋም ካስፈለገም ያንን ፈጥሮ ካልሆነም ተገቢ በሆነ መልኩ እነዚህን ፖሊሲዎች ወደማመንጨት መቅረፅና መተግበር ስራ ባፋጣኝ ሊገባ ይገባል፡፡

ዶ/ር አብይ አህመድ የተለየ ሁኔታ የወለዳቸው የተለዩ ጠቅላይ ሚኒስቴርና መሪ መሆናቸውን፤ የሕዝብ ብሶት የወለዳቸናው ኢሕአዴግን የፈጠረውን፣ ያለውንና የሚጠቀምባቸውን ሁሉ ለሕዝብ ጥቅም ሊቆጣጠሩ የሚገባ መሆኑ ለሳቸው የሕልውና፣ የማንነትና በትርጉም የሆኑት መሆኑንና ይህንን ያለመረዳትና መካድ ራስን ያለማወቅና መካድ እንደሆነ፤ የተመረጡት በኢሕአዴግ ቢሆንም ያስመረጣቸው የሕዝብ ጥያቄና ግፊት መሆኑን፤ ኢሕአዴግም በሕዝብ ጥያቄና ግፊት ተገፍቶና ተገዶ እንጂ ፈልጎ እንዳልመረጣቸዉ ሊረዱ ይገባል። የሆነውን የካደ ሕልውና አይኖረውምና እነዚህን መፈጸም ለሳቸው የሕልውና ጉዳይ ነው፡፡

ከዚህም የተነሳ ኢሕአዴግን ለዚህ ሕዝባዊ ጥያቄ መልስ መሳሪያ አድርገዉ ሊገለገሉበት ይገባል፤ ለሕዝብ ጥያቄ እንዲገዛ ሊያደርጉት ይገባል፤ የሕዝቡን ጥያቄ ለኢሕአዴግ በሚጠቅም መልኩ በማጣመም በተለመደው ነባር አካሄድ ከቀጠሉ በራሳቸው በሕዝቡና በፈጣሪያቸው ላይ ክህደት መፈፀም ይሆንባቸዋል፤ ያንን በማድረግ የፈጸሙት ክህደት ይሆናል፡፡ ምክንያቱም እስከዛሬ ድረስ የኢትዮጵያ ሕዝብ በግልፅ ጥያቄዬን ይመልስልኛል። ፍላጎቴን ያስጠብቃል።" በሚል ያመናቸው የመጀመሪያው የኢሕአዴግ መሪ ስለሆኑ፣ ያንን ካልፈፀሙ ሕዝቡን በግልፅ የካዱ የመጀመሪያ መሪም ስለሚሆኑ ነው፤ የክህደት ውጤቱ ደግሞ ሞት እንደሆነ ከዶ/ር አብይ በላይ የሚያውቅ ያለ አይመስለኝም፡፡

መልካም ዕድል፡፡

[R.B. ይሄ ጽሁፍ ትናንት በፓርላማ ከተደረገው የዶ/ር አብይ አህመድ የካቢኔ ሹም ሽር በፊት የተዘጋጅ ነው]